**Hallo**
**Basel-Stadt**

Kanton Basel-Stadt

# የባዝል ከተማ ካንቶን

ስለ ባዝል ከተማ
ፖለቲካዊ ስርዓት
ሃይማኖት
ነጻ የእረፍት ግዜ
ባህል

# ስለ ባዝል ከተማ

ካንቶን Basel-Stadt የባዝል ከተማ ካንቶን ከ26ቱ የስዊዘርላንድ ካንቶኖች ክልሎች አንዷ ናት። Basel-Stadt በጀርመንና በፈረንሳይ 3 ማዕዘን ድንበር ላይ ትገኛለች። ክልሉ ጠንካራ የሆነ ኢኮኖሚና የተለያየ አይነት ባህል የሚንጸባረቅበትና የላቀ የኑሮ ደረጃ የሚታይበት ነው።

## አሃዞች እና እውነታዎች

Basel-Stadt ሶስት ቀበሌዎችን/አውራጃዎችን/ ያቀፈ ነው። ከባዝል ማዘጋጃ ቤት እና ከሁለቱ ከሪሀን እና ቤቲንገን ፖለቲካዊ የኮምዩን አስተዳደሮችን (Gemeinden) ያጠቃልላል። ካንቶኑ ውስጥ ከ 200,000 በላይ የሚሆኑ ከ160 አገሮች የመጡ ሰዎች ይኖሩባታል። Basel-Stadt 37 ካሬ ሜትር ብቻ የቆዳ ስፋት አላት። ስዊዘርላንድ ውስጥ ትንሿ ካንቶን ስትሆን በትንሽ ቦታ ጥቅጥቅ ያለና ብዙ ሰዎች የሰፈሩበት ቦታ ነው። የክልሉ /የካንቶኑ/ የመነጋገሪያ ቋንቋ ጀርመንኛ ነው።

## ታሪክ

Basel-Stadt የተመሰረተችው በ1833 ነው ። ከተማዋ ትልቅና የሚያጓጓ ታሪክ አላት። ጥንት ከ130.000 ዓመታት በፊት ከመካከለኛው የድንጋይ ዘመን ግዜ ጀምሮ ሰዎች ሰፍረውባት ነበር። Basel ስታርቴጅያዊ በሆነ ቦታ ስለምትገኝ፣ ሮማውያን ከክርስቶስ ልደት ከ30 ዓመት በፊት የሙንስተር ኮረብታ ላይ ወታደሮቿን አስፍረው ነበር። እዛው ቦታ ላይ በአሁኑ ሰዓት የባዝል ሙንስተር ካቴድራል ይገኛል። ይህ ካቴድራል ከዚህ ቀደም የጳጳሱ ቤተ ክርስትያን ነበር፣ ቤተ ክርስትያኑም የተመረቀው በ 1019 ነው። በዚህም የተነሳ የባዝል ሙንስተሩ ካቴድራል ላይ የካንቶኑ ዓርማ የሆነው የባዝል የከዘራ ምስል የሚታየው፣ ይህም የጳጳሱን ከዘራ ነው የሚያመለክተው።
የባዝል ዩንቨርስቲ የተመሰረተው በ1460 ነው። ባዝል ወደ መጽሐፍ ህትመት እንዲሁም ወደ Humanismus /የሰብዓዊነት ጥናት/ ማዕከልነት እየጎለበተች መጣች። በ 16 ኛው ክፍለ ዘመን ከላይኛው ጣልያን ግዛትና ከፈረንሳይ ብዙ ስደተኞች ወደዛ ይፈልሱ ነበር። እነሱም የሃር ስራንና የሃር ማቅለምን ጥበብ ወደ ባዝል ይዘው መጡ። የዛሬዎቹ የመድሃኒትና የኬሚካል እንዱስትሪዎች የዚህ ውጤት ናቸው። በ1833 የBasel-Stadt እና የBasel-Landschaft ከጦርነት ግጭት በኋላ ተለያዩ። ዛሬ Basel-Stadt የባህል፣ የንግድ እና የኢኮኖሚ ማዕከል ስትሆን በዋናነትም የህይወት ሳይንስ ማዕከል ናት።

## ልምድ እና ባህል

በካንቶን Basel-Stadt ብዙ ተለምዶዎችና ባህሎች አሉን፣ እነሱም ለኛ በጣም አስፈላጊዎቻችን ናቸው። ተለምዶዎቻችንና ባህሎቻችንን ለማወቅ ፍላጎት ካላችሁ በጣም ደስ ይለናል። ከሁሉም በመጀመሪያ ደርጃ የሚከበረው ፋስናኽት (Fasnacht) በዓል ነው።. ይህ በዓል በየዓመቱ የካቲት ወይም ሚያዝያ ለሶስት ቀናቶች ይካሄዳል። ለዚያም ነው እኛ «drey scheenschte Dääg» ሶስቱ ምርጥ ቀኖች ብለን የምንጠራው። የባዝል የበልግ ትርኢት (Herbstmesse) ከ 500 ዓመት በላይ ዕድሜ ያለው ነው። እንደዚሁም የባዝል የገና ገበያ (Weihnachtsmarkt) ረጅም ጊዜ የቆየ ባህል ነው። ብዙ ሰዎች ማህበራት፣ የክለባትና የማህበራዊ ተቋማት አባላት ናቸው። የባዝል እግር ኳስ ክለብ ጨዋታ ላይ ብዙ ተመልካቾች ይገኛሉ፣ እንዲሁም በበጋ ወቅት ብዙ ሰዎች ራይን ወንዝ ላይ ይዋኛሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/kanton-basel-stadt/ueber-basel-stadt

# ፖለቲካዊ ስርዓት

ስዊዘርላንድ ውስጥ ፖለቲካዊ ስልጣን በሶስት ይከፈላል፣ ፌደራል፣ ካንቶኖች (አባል አገሮች) እና የአካባቢ አስተዳደሮች። ስዊዘርላንዳውያን በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ድምጻቸውን ይሰጣሉ።

## የስዊዘርላንድ ፌዴራላዊ ግዛት

የስዊዘርላንድ ፌዴራላዊ ግዛት የተመሰረተው ከ1848 ጀምሮ ነው። ዋና ከተማውም በርን ነው። የስዊዘርላንድ አንድነት በዘር፣ በቋንቋ ወይም በሃይማኖት የተመሰረተ አይደለም። የተለያዩ ባህሎች በነጻ ፍቃዳቸው ነው አንድ የሆኑት። በዚህ ምክንያት ነው „በበጎ ፍቃድ የተመሰረተ ሃገር“ (Willensnation). ተብሎ የሚጠራው።

## ፌደራላዊ

በስዊዘርላንድ ውስጥ ያሉት 26 ካንቶኖች እና ከ 2000 በላይ የሚሆኑት ኮሚዩኖች በፖለቲካ ራሳቸውን የቻሉና ነጻ ተቋማት ናቸው። ፌደራላዊ ናቸው የሚባሉትም በዚህም ምክንያት ነው ። እያንዳንዱ ካንቶን እና እያንዳንዱ ኮሚዩን ራሱን የቻለ የክልል መዋቅር አለው። የBasel-Stadt ካንቶን የራሱ ህገ መንግስትና መንግስት፣ ፓርላማ፣ እንዲሁም ፍርድ ቤቶች አሉት። ኮሚዩኖቹና ካንቶኖቹ ለብዙ መንግስታዊ ጉዳዮች ሃላፊነት ይወጣሉ። ለምሳሌ ያህል፣ የትምህርት ቤት ስርዓት ከካንቶን ወደ ካንቶን የተለየ አሰራር ያላቸው በዚህ ምክንያት ነው። ፌደራላዊ ህጎቹ በመላው ስዊዘርላንድ ያገለግላሉ። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ካንቶን የራሱ የሆኑ ህጎች አሉት። የካንቶኑ ህጎችም በካንቶኑ ግዛት ብቻ ነው ተፈጻሚ የሚሆኑት። እያንዳንዱ ኮሚዩን የራሱን ህግ ማጽደቅ ይችላል። ግዴታቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ ፌደራሉ፣ ካንቶኖቹና ኮሚዩኖቹ ቀረጥ/ታክስ ያስከፍላሉ።

## የስልጣን ክፍፍል

የፖለቲካ ስልጣን ጥቂት ሰዎች ላይና ጥቂት ተቋማት ላይ ብቻ መጠቅለል ስለሌለበት፣ ስለዚህም ነው የመንግስት ስልጣን በስዊዘርላንድ መንግስት አስተዳደርና በካንቶኖቹ ውስጥ ራሳቸውን የቻሉ ስልጣን ያላቸው ሶስት ተቋማት ይከፈላል። እነሱም ህግ አውጪ አካል (gesetzgebende Gewalt) ፣ ህግ አስፈጻሚ አካልና (gesetzesausführende Gewalt) የዳኝነት አካል (richterliche Gewalt). ናቸው። በካንቶን Basel-Stadt ውስጥ እነዚህን የስራ ተግባራት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሶስቱ ጽ/ቤቶች በሃላፊነት ያከናውናሉ።

- ህግ አውጪው አካል ትልቁ ምክር ቤት (Grosser Rat) (100 አባላት ሲኖሩት፣ እነሱም በየአራት ዓመቱ በህዝብ ይመረጣሉ)
- ስራ አስፈጻሚ አካል፣ የመንግስት አስተዳደር ምክር ቤት (Regierungsrat) (7 አባላት ሲኖሩት፣ እነሱም በየአራት ዓመቱ በህዝብ ይመረጣሉ)
- የዳኝነት አካል፣ በካንቶን ደረጃ የተለያዩ ፍርድ ቤቶች (Gerichte) ይገኛሉ።

ባዝል ከተማን ከሌሎች ለየት የሚያደርጋት: የባዝል ከተማ የካንቶኑ ፓርላማ፣ አስተዳደርና እንዲሁም ፍርድ ቤቶቹ የባዝል ኮሚዩኖችን ጨምረው በሃላፊነት ያስተዳድራሉ። „ሪሸን“ና „ቤቲንገን“ ሁለቱ ኮሚዩኖች አንድ የጋራ የህግ አውጪ አካል (የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ Einwohnerrat) እንዲሁም አንድ የስራ አስፈጻሚ አካል (የኮሚዩኖች ምክር ቤት፣ Gemeinderat). አላቸው። በፌደራል ደረጃ ህግ አውጪው አካል ሁለት ምክር ቤቶች አሉት: የብሄራዊ ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤት (Nationalrat und Ständerat) ናቸው ። የብሄራዊ መንግስቱ (7 አባላት) ሲኖሩት ስሙም ፌደራላዊ ምክር ቤት (Bundesrat). ተብሎ ይጠራል። በአገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ፍርድ ቤቶች አሉ። ለምሳሌ በካንቶን ፍርድ ቤቶች የተፈረዱ ውሳኔዎችን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደ የበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይቻላል።

## የዲሞክራሲ መብቶች

ስዊዘርላንዳውያን ድምጽ የመስጠትና የመመረጥ መብታቸው የተጠበቀ ነው። የፖለቲካ አካላትን በፌዴራል እንዲሁም በኮሚዩናቸውና በካንቶን ደረጃ ይመርጣሉ። ለምርጫም ቀርበውም መወዳደር ይችላሉ። በተጨማሪም ፖለቲካዊ ውሳኔዎችን በሚመለከት ህዝቡ እንዲወስን ሪፈረንደም ይደረጋል። በዚህም ነዋሪዎች በኮሚዩናቸው፣ በካንቶናቸው እንዲሁም በፌደራል ደረጃ በሚያቀርቧቸው ሐሳቦች ላይ ድምጽ በመስጠት መወሰን ይችላሉ (በቀጥታ በዲሞክራሲ)። ይህንን ለማድረግ ህዝቡ በራሱ ተነሳሽነት እንቅስቃሴ መጀመርና ማድረግ ይጠበቅበታል። በBasel-Stadt ካንቶን ነዋሪ የሆኑ የውጭ ዜግነት ያላቸው ሰዎች በመምረጥና በህዝብ ውሳኔ ላይ መሳተፍ አይፈቀድላቸውም። ይሁን እንጂ ፖለቲካዊ ጥያቄና አጀንዳ ካላቸው፣ ለአስተዳደሩ ጽ/ቤት ፊርማ አሰባስበው ማቅረብ ይችላሉ። ከዚህ ባለፈም በኮሚሽኖች፣ ጥቅም በሚያስጠብቁ ቡድኖች ወይም በማህበራቶች መደራጀትና መሳተፍ ይችላሉ።

## መሰረታዊ መብቶች

የፌደራል ህገ መንግስቱ (Bundesverfassung) ከስዊዘርላንድ የሕግ መርሆዎች ሁሉ የበላይ ነው። የፌዴራል ሕገ መንግሥቱ በአውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ኮንቬንሽን (EMRK) ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ እነዚህም ዋና አስፈላጊ የመሠረታዊ መብቶች አካል ናቸው። የሰው ልጅን በህይወት የመኖር መብት ይጠብቁለታል፣ ለምሳሌ ያክል የመኖር መብት ፣ወይም በችግር ግዜ እርዳታን የማግኘት መብቶን ይጨምራል። ከዚህም በተረፈ ግለሰቦችን ከመንግስታዊ የስልጣን ጥቃት ወይም አነስተኛ ግሩፖችን ከአብላጫው ለመጠበቅና ለመከላከል ያስችላል። ማንም ሰው ሌላውን በማንነቱ፣ በዘሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በጾታው ወይም በጾታዊ ዝንባሌው ምክንያት እንዳይገለል ዋስትና ይሰጣል። በዘረኝነት ምክንያት መገለል የሚደርስባቸው ሰዎች፣ በካንቶን Basel-Stadt ያለ ክፍያ እርዳታና ምክር ማግኘት ይችላሉ። በስዊዘርላንድ የሃይማኖት ነጻነት፣ ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት እና የፕሬስ ነጻነት ሰፍኗል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/kanton-basel-stadt/politisches-system

# ሃይማኖት

ስዊዘርላንድ በተለምዶ የክርስቲያን ሀገር ነች። በአሁኑ ግዜ ግን የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች የሆኑ ብዙ ሰዎች እዚህ ይኖራሉ። በስዊዘርላንድ የሃይማኖት ነፃነት አለ፣ እና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሃይማኖት ገለልተኛ ናቸው።

## ሃይማኖትና መንግስት (DE)

ስዊዘርላንድ በተለምዶ በክርስቲያን ሃይማኖት የተቀረጸች ሃገር ናት። ካንቶኖቹ በሃይማኖትና በመንግስት መካከል ያለውን ዝምድና ይወስናሉ። እንደ አብዛኞቹ ጀርመንኛ ተናጋሪ የስዊስ ካንቶኖች ሁሉ የBasel-Stadt ካንቶን ለአንዳንድ የሃይማኖት ማህበራት ልክ እንደ የህዝብ ተቋማት እውቅና ይሰጣሉ። ይህም ማለት መንግስት ለእነሱ የተወሰኑ መብቶችን ያስተላልፋል ማለት ነው። ለምሳሌ አባሎቻቸውን ታክስ ማስከፈል ይችላሉ። የሚከተሉት የሃይማኖት ማህበራት በBasel-Stadt ካንቶን በግልጽ የሕግ ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል: የኢቫንጀሊካል ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን፣ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እና የአይሁድ ማኅበረሰብ፣ ሌሎች አንዳንድ ተጨማሪ ማህበራትም በካንቶን ተቀባይነትን ያገኑ አሉ። እነዚህ ማህበራት በግል በሕግ የተደራጁ ናቸው።

## ሃይማኖታዊ ማህበረሰቦች በBasel-Stadt

አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት የባዝል ነዋሪዎች ከአራቱ በህግ ዕውቅና ከተሰጣቸው ማህበረተሰቦች ያንዱ አባል ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ሌላ ብዙ ሃይማኖታዊ ማህበረተሰቦች ይገኛሉ። ለምሳሌ ያክል የእስላም፣ የሂንዱ፣ የቡዲስት ወይም አዳዲስ እንቅስቃሴዎች ፣ ከነዋሪዎቹ ግማሽ ያህሉ የአንዳቸውም የሃይማኖት ማህበረሰብ አባል አይደሉም።

## የሃይማኖት ነጻነት

የስዊዘርላንድ ሕገ መንግስት የሃይማኖትን ነጻነት ያረጋግጣል። ያህም ማለት ማንኛውም ሰው ምን ዓይነት ሃይማኖትና እምነት ማመን እንዳለበት ራሱ የመወሰን መብቱ የተጠበቀ ነው። ሁሉም ሰው እምነቱን እንዲገልጽ እና እንዲያስፋፉ ተፈቅዶለታል። ማንም ሰው ማንንም ሰው ያለ ፍቃዱ ሃይማኖታዊ ማህበረሰብ ውስጥ እንዲቀላቀል ወይም በሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ እንዲካፈል ማስገደድ አይችልም። ሰዎች ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን እና በዓላትን ለማክበር እንዲሰበሰቡ ይፈቀድላቸዋል። ሰዎች በሃይማኖታቸው ወይም በእምነታቸው ምክንያት መገለል የለባቸውም።

## ሃይማኖት እና ትምህርት

ግዴታዊ ትምህርቶች ከሃይማኖት ገለልተኛ ናቸው። ይሁን እንጂ ሃይማኖታዊ ርዕሰ ጉዳዮች በክፍል ውስጥ ቦታ አላቸው። አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት «ስለ ተፈጥሮ፣ ስነ ስብ፣ ስለ ማህበረሰብ » ትምህርት ይሰጣል። እነዚህ ትምህርቶች የሚያስተምሩት ስለተለያዩ የአኗኗር ዘይቤዎች እና ባህሎች ነው። በተጓዳኝም ልጆቹ በፈቃደኝነት ሊሳተፉ የሚችሉበት የሃይማኖትና የእምነት ትምህርቶች ይሰጣሉ። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት «ስለ ስነ ምግባር ፣ ስለ ሃይማኖትና ስለ ማህበረሰብ» ትምህርት ይሰጣል። እነዚህ ግዴታዊ ትምህርቶች ናቸው። እዚህ ተማሪዎቹ ከተለያዩ ባህሎች፣ ሃይማኖቶች፣ የዓለም አቀፋዊ እይታዎች እና ማህበራዊ እሴቶች ጋር ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ጠቃሚ ክህለቶችን ይማራሉ። ከሌላ እምነት ተቋም ለመጡ ተማሪዎች ሃይማኖታዊ ማህበረሰቦች ከትምህርት ቤት ውጪ አንዳንድ ጊዜ የማስተማር እድሎችን ይሰጣሉ።

### ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/kanton-basel-stadt/religion

# ነጻ የእረፍት ግዜ

በBasel-Stadt ውስጥ ብዙ ማራኪ የሆኑ የእረፍት ግዜ ማሳለፊያና የመዝናኛ አቅርቦቶች አሉ። እነዚህም ቦታዎች አዲስ ሰው ለመተዋወቅ እና በጋራ አንድ ላይ ጊዜ ለማሳለፍ ያስችሎታል።

## ማህበራት

አብዛኞዎቹ የባዝል ከተማ ነዋሪዎች የማህበራት (Verein) አባላቶች ናቸው። የተለያየ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች እንደፍላጎታቸው ዓይነት የስፖርት ክለቦች ወይም የባህል ክለቦችና ማህበራት አሉ። ክለቦችን ወይም ማህበራትን ከተቀላቀልክ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር እንድትተዋውቅ ይረዳሃል። አብዛኞዎቹ ማህበራት ለሁሉም ሰው ክፍት ናቸው።

## አቅርቦቶች ለወጣቶች

ወጣቶች በትርፍ ጊዚያቸው ያሉትን አቅርቦቶች ቢጠቀሙ፣ ከሌሎች ከእድሜያቸው ጋር ተመጣጣኝ ከሆኑ ወጣቶች ጋር እንዲተዋወቁ ያስችላቸዋል። ፕሮጀክት ላይ መሳተፍና የራሳቸውን የግላቸውን ሃሳብ ማቅረብ ይችላሉ። ባለሙያዎች ወጣቶችን የሙያ ድጋፍ እንዲሁም አብረዋቸው በመሆን ሙያዊ ክትትል ያደርጉላቸዋል (Jugendarbeit)። በመሰረቱ አቅርቦቶቹ ከክፍያ ነጻ ናቸው።

## ሽርሽር እና ባህል

በBasel-Stadt ካንቶን ውስጥ ብዙ ጉዞዎችንና ሽርሽሮችን ማድረግና የባህል ዝግጅቶችን መጎብኘት ይቻላሉ። ብዙ ሰዎች በበጋ ወቅት በራይን ወንዝ ውስጥ ይዋኛሉ ወይም በፓርክ ውስጥ ሽርሽር ያደርጋሉ። ብዙዎች ከቤተሰቦቻው ጋር ወደ ባዝል የእንስሳት ፓርክ መሄድን ይወዳሉ። በአካባቢው የሚያምሩ የእግር ጉዞ እና የብስክሌት መንገዶች አሉ። እንደ ፍራይቡርግ፣ ብራይስጋው ወይም ስትራስቡርግ ያሉ ከተሞች በባቡር በፍጥነት መድረስ ይቻላል። በBasel Tourismus የትኞቹን የሽርሽር ጉዞዎች መሄድ እንደሚችሉ እና በየትኞቹ ዝግጅቶች ላይ መሳተፍ እንደሚችሉ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## የአካባቢ የመገናኛ ማዕከላት (DE)

የአካባቢ የመገናኛ ማዕከላት (Quartiertreffpunkte) ለሁሉም ሰው ክፍት ናቸው። ለቤተሰቦች፣ ለአረጋውያን እና ትንሽ ጀርመንኛ ለሚናገሩ ሰዎች ጭምር የሚሆኑ አቅርቦቶች አላቸው። አንዳንድ የመገናኛ መዝናኛ ማዕከላት የቤተሰብ ማዕከሎች ናቸው። የአካባቢ የመገናኛ ማዕከላት የዕለት ተዕለት ሕይወትን በሚመለከት ምክርና ድጋፍ ይሰጣሉ። በመገናኛ መዝናኛ ማዕከላት ቤተሰባዊ በዓሎችን እና ሌላ ልዩ ዝግጅቶች ለማክበር ክፍሎችን መከራየት ይቻላል።

## የበጎ ፍቃድ ስራ

በበጎ ፈቃደኝነት ስራ (Freiwilligenarbeit) በአካባቢዎ /በዙርያዎ/ ያሉትን ሰዎች እና አካባቢዎን መርዳት ይችላሉ። "በጎ ፍቃድ " ማለት፣ ለስራዎ ምንም ዓይነት ደሞዝ አይቀበሉም ማለት ነው። በጎ ፈቃደኞች በስዊዘርላንድ ውስጥ በተለይም በማህበራት ውስጥ ብዙ ተግባራትን ያከናውናሉ። የበጎ ፈቃደኝነት ስራ ለመስራት ፍላጎት አለዎት? በማህበሮች በበርካታ ጉዳዮች ውስጥ ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በባህል፣ በስፖርት፣ በማህበራዊ ጉዳዮች፣ በትምህርት፣ በእንስሳት ደህንነት፣ በአካባቢ በተፈጥሮ ጥበቃ ወይም በጤና ላይ መስማራት ይችላሉ።
በበጎ ፈቃደኝነት ስራ ላይ ለመሳተፍና ለመሰማራት መረጃ እዚህ ማግኘት ይችላሉ:

- የበጎ ፍቃድ ሥራ ኤክስፐርት ቢሮ GGG Benevol
- የስዊዘርላንድ ቀይ መስቀል በBasel-Stadt (SRK)
- የባዝል ከተማ ካሪታስ

በጥገኝነት ጠያቂዎች እና በስደተኞች መስክ ለመሰማራት አስፈላጊ መረጃ፡-

- በጥገኝነት ጠያቂዎች መስክ የበጎ ፍቃድ ሥራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት (KOFF)
- የስዊዘርላንድ የስደተኞች እርዳታ

## በስፖርት፣ በባህል እና በትምህርት ዝግጅቶች ላይ ቅናሾች

"KulturLegi" የሚል መታወቂያ የሚያገለግለው ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ሰዎች ነው። KulturLegi ካለዎት ለስፖርት፣ ለባህል እና ለትምህርት ዝግጅቶች የሚከፍሉት ክፍያ አነስተኛ ነው። KulturLegi ለማግኘት ካሪታስ ማመልከት ይችላሉ። ካሪታስ ስለ KulturLegi ስለሁኔታው መረጃ ይሰጥዎታል፣ በተጨማሪም የሚገባዎት መሆኑንና አለመሆኑን ያረጋግጣል። እንዲሁም የቤተሰብ ካርድ (Familienpass) እና FamilienpassPlus ካርድ ይሰጣል። እነዚህ ካርዶች የሚያገለግሉት በሰሜናዊ ምዕራብ ስዊዘርላንድ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ነው። ለልጆች፣ ለወጣቶች እና ለጎልማሳ ወጣቶች ብዙ ተጨማሪ ቅናሾች እና ያለ ክፍያ ነጻ አቅርቦቶች አሉ፣ ለምሳሌ "colourkey" ወይም የእረፍት ካርድ (Ferienpass). በKulturLegi የቤተሰብ ካርድ ወይም በcolorkey ብዙ አቅርቦቶች ቅናሽ ናቸው። ስለዚህ ጉዳይ በሚመለከት በበይነ መረብ በኢንተርኔት ላይ የበለጠ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/kanton-basel-stadt/freizeit

# ባህል

ባዝል ከተማ ውስጥ ብዙ የባህላዊ ዝግጅቶች ይካሄዳሉ። ብዙ ገንዘብ ከሌለዎት፣ ያለ ክፍያ ወም በነጻ የመጠቀም ብዙ አማራጮች አለዎት።

## ሙዚየሞች / ኢግዚቢሽኖች

ወደ አርባ የሚጠጉ ሙዚየሞችና ኤግዚቢሽኖች ዝግጅቶችን ያቀርባሉ። በተጨማሪም ብዙ ትናንሽ ጋለሪዎች እና አማራጭ የጥበብ ስራ ውጤቶችን ማሳያ ቦታዎችን መጎብኘት ይችላሉ። ለሕዝብ ክፍት በሆኑ ቦታዎች ብዙ የጥበብ ሥራዎችን መጎብኘት ይቻላል።

## ሙዚቃ / ዳንስ / ቲያትር / ስነ ጽሑፍ (DE)

በBasel-Stadt ካንቶን ውስጥ ብዙ ባህላዊ ዝግጅቶች ይካሄዳሉ። በTheater Basel ውስጥ ኦፔራ፣ ድራማ እና ባሌት እንዲሁም በKaserne ዘመናዊ ሙዚቃ፣ ዳንስ ወይም ቲያትር በማየት መደሰትይችላሉ። እንደ Vorstadttheater ወይም የSommercasino ያሉ ትናንሽ ቦታዎችም አሉ። በበጋ ወቅት ብዙ የውጪ ትርኢቶች እና ፌስቲቫሎችን መጎብኘት ይችላሉ። አንዳንድ ዝግጅቶችም ከክፍያ ነጻ ናቸው።

## አርክቴክቸር

በባዝልና በአካባቢው ብዙ ዘመናዊ የአርክቴክቸር ስራዎችን ማድነቅ ይቻላል። ለምሳሌ በአርክቴክት ሬንዞ ፒያኖ የተሰራው Fondation Beyeler በራይን ማየት ይቻላል። በባዝል መሃል ከተማ በChrist & Gantenbein አርክቴክቸር ቢሮ የKunstmuseums Basel አዲስ ህንፃ ግንባታ ወይም በHerzog & de Meuron አርክቴክቸር ቢሮ የStadtcasinos Basel ቀጣይ ማስፋፊያ ግንባታ ይታያል።

## ባህልን ማበረታቻዎች

በሙያዎ አርቲስት ከሆኑ ለፕሮጀክትዎ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከት ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል የገንዘብ ድጋፍ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል በባህል ቢሮ ድረ ገጽ ላይ የበለጠ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## ከክፍያ ነጻ እና ቅናሽ አቅርቦቶች

ብዙ ሙዚየሞችና ባህላዊ ዝግጅቶች የሚደረግባቸው ቦታዎች ልዩ የሆነ የዋጋ ቅናሽ አቅርቦቶች አላቸው። ለምሳሌ ያህል በተወሰኑ ወቅቶች ነጻ መግቢያ ወይም ያነሰ ክፍያ ይጠይቃሉ። ለተወሰኑ ሰዎች መግቢያ አብዛኛውን ግዜ ቅናሽ ወይም ነጻ ነው። በተጨማሪም ክፍያ የሌላቸው ነጻ ዝግጅቶች ወይም ፌስቲቫሎች ለህዝብ ክፍት በሆኑ ቦታዎች ይዘጋጃሉ። ብዙ ማህበራት (Vereine) እና ድርጅቶች ስደተኝነትን በተመለከተ ባህላዊ ዝግጅቶችና አቅርቦቶች አላቸው። በKulturLegi የቤተሰብ ካርድ (Familienpass) ወይም በcolorkey ላላቸው ሰዎች ብዙ ቅናሽ አቅርቦቶች አሉ። ብቻዎትን ወደ ሙዚየም መሄድ አይፈልጉም? በግሩፕ ወይም በTandem ጥንድ ለሆኑ ሰዎች የተለያዩ ቅናሽ አቅርቦቶች አሉ። "Tandem" ማለት: ከሌላ አንድ ሰው ጋር በጥንድ ዝግጅቱን የሚካፈሉ ከሆነ ነው።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/kanton-basel-stadt/kultur